# በሰሜን ጎንደር የአስቸኳዋይ ጊዜ አዋጁ በተደነገገ ማግስት በመንግስት ወታደሮች ላይ ጥቃት መፈጸሙ ተነገረ

February 18, 2018

በሰሜን ጎንደር በመንግስት ወታደሮች እና በአከባቢው በትግል በሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ሃይሎች መካከል የተኩስ ልውውጥ እንደነበረ ተገለጸ።

በጎንደር ከተማ ቀበሌ 09 አካባቢም ቦንብ ተወርውሮ ፍንዳታ ተከስቷል። በቦታው በነበሩ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ላይ ቦንቡ እንደተወረወረ ምንጮች ገልጸዋል።

የአስቸኳዋይ ጊዜ አዋጅ በመላው አገሪቷ በየካቲት 9 ቀን 2010ዓም ቢደነገግም በቀጣዩ ቀን (በየካቲት 10 ቀን 2010ዓም) በሰሜን ጎንደር በሰፈሩ የመንግስት ወታደሮች ላይ ጥቃት እንደደረሰ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በአርማጭሆ አብድራፊ ከተማ ለነጻነት በትግል እየተንቀሳቀሱ ያሉ ሃይሎች በመንግስት ወታደሮች ላይ በሌሊት በከፈቱት ተኩስ ቁጥራቸው የበዛ የመንግስት ወታደሮች ጉዳት እንደደረሰባቸው እየተነገረ ሲገኝ ከመንግስት በኩል ጥቃቱን በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ የለም።

ሌሊቱን የተኩስ ድምጽ መስማታቸውን የአከባቢው ሰዎች በመግለጽ ወታደሮች እና በደህንነት ዘርፍ ላይ የሚሰሩ የመንግስት አገልጋዮች ተጠልለውበት በነበሩ መኖሪያ ቤቶች ላይም ጥቃት እንደተፈጸመ ተናግረዋል።

በደህንነት ዙሪያ የሚያገለግሉ የተወሰኑ ግለሰቦች በወታደሮች ታጅበው ወደ ሁመራ መንገድ በተሽከርካሪ ሲያቀኑ መታየታቸውንም የአከባቢው ምንጮች ገልጸዋል።

በሰሜን ጎንደር በምትገኘው አብደራፊ ከተማ በመንግስት ወታደሮች ላይ ጥቃት መፈጸሙ በመላ አገሪቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተደነገገው የአስቸኳዋይ ጊዜ አዋጅ ዘለቄታዊ ሰላምን እንደማያመጣ ለማሳየት በሚል እሳቤ ሳይሆን እንዳልቀረ አስተያየት ሰጪዎች ግምታቸውን እያሰፈሩ ይገኛሉ።